# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (አንድነት) ልሣን *

ቅጽ 44 ቁ.1 ሚያዝያ 2016

## ሕዝባዊ መነሳሳትን የሁሉም ኢትዮጵያ ለምትሆን የተረጋጋች አገር ማድረግ ያስፈልጋል

አራተኛ ወሩን ያስቆጠረው በአዲስ አበባ ገጠራማ አካባቢ ተጀምሮ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ፤ ባመዛኙ በወጣት ኦሮሞ ኢትዮጵያውያን ተካፋይነትና መስዋዕትነት እየተካሄደ ያለው እንቅስቃሴ የቅርብ ምክንያቶችና መሠረታዊ ምክንያቶች ተብለው በሁለት ሊከፈሉ በሚችሉ አንቀሳቅሾች ሊታይ ይችላል።

ዋነኛው እንቅስቃሴውን የለኮሰው የቅርብ ምክንያት፤ የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ተብየው በአዲስ አበባ አስተዳደርና አገዛዙ የኦሮሞ ክልላዊ አገዛዝ በሚለው ኗሪዎች መካከል የተፈጠረው ውዝግብ ነው። የአዲስ አበባ አጎራባች ገጠራማ ቦታዎች ኗሪዎች የእርሻና የመኖሪያ ቦታቸው በአዲስ አበባ አስተዳደር ያላግባብ ተቀምቷል፤ ተዘርፏል፤ በአገዛዙ ቱባ ባለሥልጣኖችና በሃብታም ወዳጆቻቸው የመሬት ቅርምት ተደርጓል የሚል ነው።

መሠረታዊ ምክንያቶቹ ግን ሥር የሰደዱ፤ የሰነበቱና የከረሙ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ናቸው። እነዚህም፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ በስም ብቻ ፌደራላዊ አስተዳደር መሠረትኩ እያለ የቡድንና የግለሰብ መብቶችን ደፍጥጦ፤ ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግሥት አለኝ እያለ የህግ የበላይነትን አሽቀንጥሮ ጥሎ፤ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን አፍኖ፤ በእግራቸው መቆም የቻሉ የፖለቲካ ድርጅቶችን አሳድዶ፤ በትኖና መሪዎቻቸውን አሥሮ፤ የነፃ ጋዘጦችና ኅትመቶችን ከልክሎና ጋዜጠኞችን በሃሰት ውንጀላ እሥር ቤት አጉሮ፤ ለሃይማኖታቸው ነፃነት በሰላማዊ መንገድ የታገሉ የእስልምና ሃይማኖት መሪዎችንና መፍትሄ አፈላላጊ የኮሚቴ አባሎችን አሥሮ፤ አገሪቱ ለአገዛዙ አባሎችና ለሸሪኮቻቸው የጥገት ላም ሆና እየታለበች፤ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን የበይ ተመልካች በመሆን ካሉት በታች ከሞቱት በላይ ሆነው የሚታዩባት ኢትዮጵያ በዘመነ-ህወሓት የሲያል ምድር መሆኗ ነው።

ከላይ የጠቀስናቸው ችግሮች በደቡብ፤ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ብቻ የሚታዩ ችግሮች አይደሉም። በነዚህ አካባቢዎች እንቅስቃሴዎች እንደተጀመሩ፤ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ክፍልም የቅርብና መሠረታዊ ምክንያቶች ያሉት እንቅስቃሴ እየተካሄደ ይገኛል። ይህ የወልቃይት ጠገዴን ወደ ትግራይ ክልል መጠርነፍ የሚቃወም የረጅም ጊዜ የተቃውሞ ትግል፤ በተለይም በአሁኑ ወቅት የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ እንቅስቃሴውን ለመከፋፈል የገፋው አዲስ የቅማንት የማንነት ጥያቄና "ቅማንትና አማራ" ለሚለው ለህወሓት የከፋፍለህ አዳክመው ስትራተጂ ምላሽ የትግራይ ክልል የሚባለውን አመራሮች ባስጨነቀ በእልህና በምሬት የታጀበ ሕዝባዊ ተቃውሞ በወልቃይትና በጎንደር ከተማ ባሉ አካባቢዎች የታየበት ነው። ይህ የሰሜን ምዕራብ አካባቢ እንቅስቃሴ እንደ ደቡብ ኢትዮጵያው እንቅስቃሴ መሬትን፣ ፌደራሊዝምን በተለይም ደግሞ መሬትን ቆርሶ ለሱዳን መስጠትን ተግዳሮት ተንተርሶ የታየ የቅርብ ምክንያት ሲሆን፤ መሠረታዊ ምክንያቶቹ ግን በ25 ዓመቱ ዘመነ-ህወሓት ሥር የሰደዱ፣ ያረጁና ያፈጁ ከላይ ያነሳናቸው ምክንያቶች ናቸው። እነዚህ መሠረታዊ ምክንያቶች፣ ማለትም የህግ የበላይነት አለመኖር፣ አገሪቷ በህወሓት/ኢህአዴግ አምባገነናዊ ክርን መዳሸቅ፣ በሃብታምና በድሃ መካከል ያለው የኑሮ ልዩነት መስፋት፣ እጅግ የተንሰራፋ ጠባብ ቡድነኝነትና አድሎ፣ ወጣቶች በተማሩበት መስክ ሥራ ማጣት፣ ራሱ ገዥው ፓርቲ እንዳመነው በአገሪቱ ደላላና ሙስና የተንሰራፋባት መሆኗ ተደማምረው የወለዱት ተጨባጭ ሁኔታ ነው። ይህ ብልሹ አገዛዝ በሰሜንና በደቡብ ኢትዮጵያ የተወሰነ ሳይሆን፤ መላዋን ኢትዮጵያ ከመቀሌ እስከ ሞያሌ፤ ከደሴ እሰከ አርባ ምንጭ፤ ከሐረር እስከ ባህርዳር የተሰራጨ ተውሳክ ነው።

የኢትዮጵያን የወደፊት ዕጣና አቅጣጫ የሚወስኑትም እነዚህን መሠረታዊ ችግሮች ለማቃለልና ለመፍታት መቻላችን ላይ ነው ቁልፉ ያለው። የቅርብ ምክንያቶች መፍትሄ የሚያመጡ ቢሆንማ ኖሮ በጥር ወር መጀመሪያ ላይ ህወሓት/ኢህአዴግ ለደቡብ ኢትዮጵያ የወጣቶች እንቅስቃሴ የቅርብ ምክንያት የሆነውን የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን "ሰርዣለሁ" ሲል እንቅስቃሴው ባቆመ ነበር። ሆኖም የአገዛዙ ልፈፋ ሳያግደው፤ እንቅስቃሴው አቅምና ስፋቱ እየጨመረ ወደ ሌሎች ቦታዎች በመዛመቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ተብዬው "አስከፊ እርምጃ" እንደሚወስድ የገለጸበት ሁኔታ ላይ እንደተደረሰ ታይቷል።

ህወሓት/ኢህአዴግ በሰሜንና በደቡብ ኢትዮጵያ የተከሰቱትን እንቅስቃሴዎች በውሉ የተረዳቸው አይመስልም። ለነገሩ አምባገነኖች ሥልጣን ላይ ሙጭጭ ብለው ለመቆየት ባላቸው ፍላጎት ምክንያት ለመሠረታዊ ችግሮች ምላሽ መፈለግ ማለት የሚወዱትን

ሥልጣን የሚቀናቀን ሁኔታ መፍጠር ስለሚሆን ለጊዜው ፋታ የሚሰጣቸውን መፍትሄ ብቻ ወስደው ጊዜ ለመግዛት እንደሚሞክሩ የታወቀ ነው።

ከላይ በጠቀስናቸው መሠረታዊ ምክንያቶች ተጸንሶ የተወለደውን የታክሲ ነጂዎች እንቅስቃሴም አንዱን ወይም ሌላውን የታክሲ ህግ በመሰረዝ ወይም በማሻሻል፤ እንደ አዲስ አበባው ማስተር ፕላን መፍትሄ ሊፈጥሩለትና የሥራ ማቆም አድማውን ለማቀዝቀዝ እንደሞከሩም ታይቷል። የኢትዮጵያ መሠረታዊ ችግሮች ግን አሁንም እንዳፈጠጡና "የመፍትሄ ያለህ" እያሉ በመጮህ ላይ ይገኛሉ።

ህወሓት/ኢህአዴግ በተወሰነ ወቅት የመልካም አስተዳደር ችግር እንዳለ በመገናኛ ብዙሃን የገለጸው ሕዝቡ አገዛዙ ችግሩን ተረድቷል፣ መፍትሄም ያመጣል የሚል አጉል ተስፋ እንዲኖረው ለማድረግ የተደረገ ሙከራ ነው። አገዛዙ የሀገራችንን ችግር ስፋቱንና ጥልቀቱን በውል የተገነዘበው ስላልሆነም መፍትሄ ማምጣት አይችልም፤ አገሪቱንም ወደባሰ ችግር ውስጥ ሊዘፍቃት ይችላል። የመልካም አስተዳደር እጦት ማለት ከላይ የጠቀስናቸው አገሪቷ ያሉባት ችግሮችና የእንቅስቃሴዎቹ ሁሉ መሠረት የሆኑት ምክንያቶች ናቸው። ለህግ የበላይነት መጥፋት፤ ለሙስና፤ ለዜጎች በውሸት ሰነድ እሥር ቤቶች መማቀቅ፤ የመፈክር ጋጋታና በስብሰባ ማጨናነቅ ከቶውንም መፍትሄ አያመጡም። መፍትሄው አገራችን ሰላም፣ መረጋጋትና ብልጽግና የሰፈነባት፤ እኩልነት በሁለንተናዊ መልኩ የሚተገበሩባት፤ ብሄር/ብሄረሰቦችና ጎሣዎች ባህላቸውና ቋንቋቸው አንድነቷ በተጠበቀ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከበሩበት፤ የግለሰብ መብቶች ማለትም የመናገር፤ የመሰብሰብ፤ የመደራጀትና ከቦታ ወደቦታ የመንቀሳቀስና በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል የመኖርና ንብረት የማፍራት መብቶች የሚከበሩባት ሀገር ማድረግ ነው።

በደቡብ ኢትዮጵያ የሚካሄደውን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ቀደም ብሎ በአዲስ አበባ ከተማ ከሁለት ዓመት ላላነሰ ጊዜ ከተካሄደው የሞስሊም ኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ነፃነት ደሞክራሲያዊ ትግል ጋር የሚያመሳስለው ሰላማዊና ሕዝባዊ መሆኑ ነው። በደቡብ ኢትዮጵያ እንቅስቃሴ ውስጥ ባመዛኙ ኦሮሞ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍለዋል። ከ200 በላይ ወጣቶች ሕይወታቸው ተቀጥፏል። ከሟቾቹ መካከል አንዳንዶቹ ቤተሰባቸውን እነሱ ብቻ የሚጦሩና በሽተኛ ወላጆቻቸውን የሚንከባከቡ ይገኙባቸዋል። በሺዎች የሚቆጠሩ በእሥር እየተሰቃዩ ይገኛሉ። ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ብሶታቸውን ስላስተጋቡ ብቻ በወጣቶቹ ላይ ያረፈው የአገዛዙ የፈሪ ዱላ በምርጫ 1997 ከተካሄደው ግድያና ሌሎችም ህወሓት/ኢህአዴግ ከወሰዳቸው ግድያዎች ጋር

ያመሳስለዋል። በዚህ ግድያ የተሳተፉና ትዕዛዝ የሰጡ ሁሉ በሃላፊነት እንዲጠየቁ፤ እንዲሁም በእሥር እየማቀቁ የሚገኙትም በአስቸኳይ እንዲፈቱና አገዛዙ ይቅርታ እንዲጠይቃቸው ይገባል።

በደቡብ ኢትዮጵያ በአመዛኙ በኦሮሞ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች አነሳሽነት የታየው እንቅስቃሴ ለምን በሌሎች አካባቢዎች አልታየም? ይላሉ አንዳንዶች። ጥያቄው መልካም ሆኖ አቅጣጫውን የሚስተው ግን ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ውስጥ አንዱን ብቻ ነጥሎ ለምን "አማሮች" አልተቀላቀሉም? ሲል ነው። ይህ ወዳጆችን ነጣጥሎ አንዳንዶችን በአንድ ሠፈር ሌሎችን በሌላ ሠፈር መመደብ በህወሓት/ኢህአዴግ የምንጠላውን ከፋፋይና የዘር ፖለቲካን ማራመድ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ከላይ እንዳልነው በህወሓት/ኢህአዴግ 25 ዓመት ብልሹ አገዛዙ፤ መላ የኢትዮጵያ ሕዝብን የበደለና ያሰቃየ በመሆኑ የህገራችን ሥርየት የሚገኘው ሁላችንም ተባብረን በምናካሂደው ዴሞክራሲያዊ ትግል ነው። ስለዚህ በአሁኑ ሰዓት ትግሉን አጠንክሮ ለማስቀጠል የተቃዋሚዎች ኅብረት ወሳኝ ነው።

አንድ እንቅስቃሴ ጎልቶ እንዲወጣ አስተዋጽዖ ከሚያደርጉት ውስጥ የቅርብ ምክንያቶች ሊጠቀሱ እንደሚችሉ ከላይ አይተናል። ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች በተምኔትና በፍላጎት ብቻ እንደማይመጡ በሀገራችን ታሪክ ከየካቲት አብዮት መፈንዳት ጀምሮ አይተናል፤ የሌሎች አገሮችንም ታሪክ አንብበናል፤ ሰምተናል። በሌላ በኩል ደግሞ "ኦሮምያ ለኦሮሞዎች" ብቻ የሚል መፈክርና ፅንሰ-ሃሳብም አድምጠናል። ይህም እንደላይኛው ሁሉ የተሳሳተ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪካዊ ትስስርና የጋራ ታሪክ የሚክድ፤ አግላይና ፀብ ጫሪ መፈክር ነው። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሚኖርበትና በተወለደበት የአገሪቷ ክፍል ባዕድ ሊሆን አይገባውም፤ በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ተዘዋውሮ የመሥራትና ጥሪት የማፍራት መብቱም በህግ የተጠበቀ መሆን አለበት እንጂ ኋላቀር ወደሆነው ወደ ዘመነ-መሳፍንት መሰል ሥርዓት ልንመለስ አይገባም። የወደፊቷን ኢትዮጵያ በጋራና በእኩልነት መገንባት ከሁሉም ጎሣዎችና ብሄር/ብሄረሰቦች ይጠበቃል።

የማንነትና የእኔነት ፖለቲካ (identity politics) የአንድን ጎሣ፤ የአንድን ፆታ፤ የአንድን የተጨቆነ ክፍል የመብት ጥያቄ በማጉላትና በማስረገጥ አዎንታዊ ሚና እንዳለው ቢታወቅም በአንፃሩ ደግሞ ተፎካካሪነትን በመፍጠር፤ "እኔና እናንተ" እያለ የባላንጣነትን ስሜት ፖለቲካው ውስጥ በመዶል አደፍራሽና ጎጂ ሚናም ስለሚጫወት፣ በሚዛን፣ የህግ የበላይነትን መሠረት ባደረገ፣ የሀገሪቱን ሃብት በተስተካከለ መንገድ ባካፈለ፣ የሀገሪቱን

ፖለቲካ በእውነተኛ ፌደራላዊ ሥርዓት ባዋቀረ ሥነ-መንግሥት ማስተዳደር ይገባል። ቋንቋንና ጎሣን ብቻ መሠረት ያደረገ ፌደራሊዝም ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። ይህን ጉዳት ደግሞ በኢትዮጵያችን ባለፉት 25 ዓመታት ስላየነው ሌሎች አገር ገንቢና አስማሚ የሆኑ የፌዴራሊዝም አወቃቀሮችን መተግባር ያስፈልጋል። አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ለዓለም ሥልጣኔ ያበረከትነውን የግዕዝ ፊደላት የሚጠቀሙ በመሆናቸው በርካታ ኢትዮጵያውያን ሁለትና ከዚያ በላይ የኢትዮጵያን ቋንቋዎች ለመናገርና ለመጻፍ በር ከፍቶላቸዋል። ሌላው የአገሪቱ ክፍለ ግዛቶች ክፍፍልና አስተዳደር መልክዓምድርን የተከተለ፣ ለምሳሌ ወንዞችን፤ ለኢኮኖሚ ዕድገትና ለአስተዳደር ቅልጥፍና መመቸትን፣ ታሪካዊ አሠፋፈርን ግምት ውስጥ ያስገባና ቋንቋንም እንደ ብቸኛ መመዘኛ ሳይሆን ከግምት ውስጥ ያስገባ መመዘኛ በማድረግ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ድርጅቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የህግና የሕዝብ ሠፊራ ምሁራንን...ወዘተ ያካተተ የሊቃውንት ጉባዔ ሊመክርበትና ሊወስንበት የሚገባው ጉዳይ ነው ብለን እናምናለን።

ኢ.ሕ.አ.ፓ ከተመሠረተበት ከ44 ዓመት ጀምሮ ለብሄሮችና/ብሄረሰቦች መብቶች ያላሰለሰ ትግል አካሄዷል፤ አስተምሯል። የብሄር ጥያቄ በሀገራችን ውስጥ ካሉት ችግሮች አንዱ እንደሆነ ግንዛቤ እንዲወሰድ የድርሻውን አበርክቷል። ጥያቄው በአንዲት ደሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲፈታ ያቀረባቸው የመፍትሄ ሃሳቦች ኢ.ሕ.አ.ፓ በአንዳንዶች በጠላትነት እንዲታይ አስተዋጽዖ አድርጓል። በጠላትነት መታየት ብቻ ሳይሆን መስዋዕት እንዲከፍልም አድርጎታል። ለዚህ ዋናው ማስረጃ ህወሓት በኢ.ሕ.አ.ፓ/ኢ.ሕ.አ.ሠ ላይ በትግራይና በወልቃይት የከፈተበት ጦርነት ነው። በተያያዥ ሻዕቢያም፤ ኦነግም፤ በአብዮቱ ወቅት የነበረው የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጭ ድርጅት ተብሎ ይጠራ የነበረው ድርጅትም የተረባረቡበት ድርጅት ነው።

የዛሬው የኢትዮጵያ ፌደራሊዝም፤ ደርግን የተኩት ህወሓት፤ ኦነግና ሻዕቢያ በማን አለብኝነት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የጫኑት ኢ-ዴሞክራሲያዊ ፌዴራሊዝም በመሆኑ ሊሠራ አለመቻሉ ታይቷል። የተሻለ መንገድ እንዳለ ከላይ አሳይተናል። ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ የኢትዮጵያን ፖለቲካ ሰንገው የያዙትን መሠረታዊ ችግሮች የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ኢትዮጵያዊው ወጣት በጋራ እንዲቀርፍ ታሪክ ጥሪዋን ታቀርባለች።

የህግ የበላይነትና መልካም አስተዳደር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች ናቸው!